# የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

# Commercial Bank of Ethiopia

## ጋዜጣዊ መግለጫ

## የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የ2020/21 ግማሽ አመት ዕቅድ አፈጻጸምን አስመልክቶ የተዘጋጀ

### 1. መግቢያ

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሀገራችን የባንክ ኢንዱስትሪ ውስጥ የመሪነት ሚናውን እንዳስጠበቀ ላለፉት 78 አመታት መጓዝ የቻለ ባንክ ነው፡፡ የሀገሪቱን የልማት ፕሮጀክቶችና አጠቃላይ የልማት እንቅስቃሴ በፋይናንስ በመደገፍ፣ የባንክ አገልግሎት በመላ ሀገሪቱ በማስፋፋትና አዳዲስ በቴክኖሎጂ የተደገፉ የባንክ አገልግሎቶችን በማስተዋወቅ ረገድ ግንባር ቀደም ሚና እየተጫወተ ይገኛል፡፡

የሀገሪቱን ፈጣን ልማት ተከትሎ በመንግስትና በግሉ ዘርፍ ኢንቨስትመንት የሚካሄዱ የልማት ፕሮጀክቶች በከፍተኛ ሁኔታ እያደጉ በመምጣታቸው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክም ይህንኑ የሚመጥን ምላሽ በመስጠት ላይ ነው፡፡

በተለይም ባንካችን እ.ኤ.አ በ2025 ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የንግድ ባንክ ለመሆን ራዕይ ስላስቀመጠ ለዚሁ ስኬት በትጋት እየሰራ ይገኛል፡፡ የ2021 በጀት አመት የግማሽ አመት ክንውንም ራዕያችንን ከማሳካት አንፃር በትክክለኛው መስመር ላይ መሆናችንን አመላካች ነው፡፡

የባንካችን አመታዊ የዕቅድ አፈጻጸምና የስትራቴጂ ትግበራ ሪፖርቶች እንደሚያሳዩት ባንኩ ራዕዩን ለማሳካት በሚያስችል ቁመና ላይ መገኘቱን ነው፡፡ በያዝነው የፈረንጆች አዲስ አመት የወጡ አለም አቀፍ የጥናት ሪፖርቶች ይህንኑ የሚያጠናክሩና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በአፍሪካ ከሚገኙ ጠንካራና ቀዳሚ ባንኮች መካከል አንዱ መሆኑን የሚያመላክቱ ናቸው፡፡ አፍሪካ

ቢዝነስ እና ዘአፍሪካ ሪፖርት ባወጡት የጥናት ዘገባም ይህንኑ አመልክተዋል፡፡ ባንካችን ካሳለፍነው አመት ጀምሮ ለሀገራችን ትልቅ ፈተና የነበረውን የኮቪድ-19 በሽታ በመቋቋም መልካም አፈፃፀም ካሳዩ ባንኮች አንዱ መሆን የቻለ ሲሆን፣ አፍሪካ ውስጥ ከሚገኙ 100 ምርጥ ባንኮች መካከል የ17ኛ፣ ከምስራቅ አፍሪካ ደግሞ 1ኛ ደረጃ በመያዝ አመቱን አጠናቋል፡፡

## 2. የተቀማጭ ገንዘብ አሰባሰብ

ከባለፉት ጊዜያቶች በተሻለ በዚህ ግማሽ አመት የተለያዩ ስትራቴጂዎችን በመተግበር የህብረተሰቡን የቁጠባ ባህል ለማበረታታት፣ ከማህበራትና ከሌሎች ተቋማት ጋር ያለንን ግንኙነት ለማሻሻል እና የባንኩን የአገልግሎት አሰጣጥ ለማዘመን የሚረዱ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ ከእነዚህ ጥረቶች  ዋና ዋና ግቦች መካከል አንዱ የባንኩን የተቀማጭ ሒሳብ ማሳደግ  ነው፡፡ እነዚህ ጥረቶች በዚህ ግማሽ አመት መልካም ስኬት ያስገኙ ሲሆን፣ የባንኩን የተቀማጭ ገንዘብ በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ ችለዋል፡፡ በዚህ መሰረት፡-

- በ2020/21 የመጀመሪያ ግማሽ ዓመት በተደረገው የሃብት ማሰባሰብ እንቅስቃሴ የተሰበሰበው ተጨማሪ  የተቀማጭ ገንዘብ 83.2 ቢሊዮን ብር ሲሆን፣ ክንውኑም 221 ከመቶ ሆኗል፡፡
- የባንኩ አጠቃላይ የተቀማጭ ገንዘብ ክምችት 678.7 ቢሊዮን ብር ማድረስ የተቻለ ሲሆን፣ ይህም ከዕቅድ በላይ የ107 ከመቶ ክንውን ያሳያል፡፡

## 3. የውጭ ምንዛሬ ግኝት

የሀገሪቱን የልማት ጥያቄ በአግባቡ ለመመለስ እንዲቻል እንደተቀማጭ ገንዘብ ማሰባሰብ ሁሉ የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ለማሳደግ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

- ባንኩ በግማሽ በጀት  ከሀዋላ፣ ከውጭ ምንዛሬ እንዲሁም ከወጪ ንግድ ከ1.4 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር በላይ ለማሰባሰብ ችሏል፡፡
- ከተሰበሰበው የውጪ ምንዛሬም ለተለያዩ የግልና የመንግስት የልማት ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያና የገቢ ንግድ እንዲውል የ2.5 ቢሊዮን ዶላር አቅርቦት ድርጓል፡፡

## 4. የብድር ስርጭትና አሰባሰብ ክንውን

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሀገራችን ለሚከናወኑ የልማት ፕሮጀክቶች ዋነኛ የፋይናንስ ድጋፍ አቅራቢነቱ ይታወቃል፡፡ በ2020/21 የመጀመሪያ ስድስት ወራትም ይህን ተግባር ያከናወነ ሲሆን፣ የብድር አቅርቦትና አሰባሰብ አፈፃፀሙም እንሚከተለው ቀርቧል፡፡

- በግማሽ አመቱ ለልዩ ልዩ ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችና የንግድ ተቋማት የሚውል የ47.2 ቢሊዮን ብር አዲስ ብድር ለመስጠት ችሏል፡፡
- በተጨማሪም በግማሽ አመቱ 26.1 ቢሊዮን ብር መሰብሰብ ተችሏል፡፡

## 5. አጠቃላይ ትርፍና ሀብት  አፈጻጸም

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ባለፉት ስድስት ወራት ከነበረው አጠቃላይ ክንውን ከታክስ በፊት የ7.4 ቢሊዮን ብር ትርፍ ማግኘት ችሏል፡፡

በ2020/21 የመጀመሪያ ግማሽ አመት የባንኩ ጠቅላላ ሀብት 903.6 ቢሊዮን ብር ማድረስ ተችሏል፡፡

## 6. የባንክ አገልግሎት ተደራሽነት እና የኤሌክትሮኒክ ባንኪንግ አፈጻጸም

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አገልግሎትን ተደራሽ ለማድረግ እንደባለፉት ጊዜያት ሁሉ ጠንክሮ እየሰራ ይገኛል፡፡ በዚህ ግማሽ ዓመትም በቅርንጫፍ ባንክ ከፈታ እና በኤሌክትሮኒክስ የባንክ አገልግሎቶች አማካኝነት በርካታ አዳዳስ ደንበኞች ማፍራት የተቻለ ሲሆን፣ ለነባር ደንበኞች አገልግሎቶቻችን በቅርበት የሚገኙ፣ እንግልት የሚቀንሱና ለደንበኞቻችን እርካታ የሚሰጡ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት በ2020/21 የመጀመሪያ ስድስት ወራት ውስጥ፡-

- 42 አዳዲስ ቅርንጫፎች በመክፈት የባንኩን ቅርንጫፎች ብዛት 1,646 ማድረስ ተችሏል፡፡
- 1.4  ሚሊዮን የኤ.ቲ.ኤም ካርድ ፣ 9,200 የኢንተርኔት ባንኪንግ እና  1.8 ሚሊዮን የሞባይል ባንኪንግ አዳዲስ  ተጠቃሚ ደንበኞችን ማፍራት ተችሏል፡፡

- 2.6 ሚሊዮን የሲቢኢ ብር ደንበኞች እና ከ7,600 በላይ የሲቢኢ ብር ወኪሎችን መመልመልና ወደ ስራ ማስገባት ተችሏል፡፡
- በአጠቃላይ በነበረው ተደራሽነትን የማስፋት እንቅስቃሴ 2.5 ሚሊዮን አዳዲስ ሂሳቦችን በመክፈት ዕቅዱን ማሳካት የተቻለ ሲሆን፣ የባንኩ ደንበኞች ቁጥርም 27.5 ሚሊዮን ደርሷል፡፡

## 7. ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት (CBE NOOR) አፈፃጸም

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ 61 ሙሉ በሙሉ ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት ብቻ የሚሰጡ ቅርንጫፎችን ከፍቶ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡ በአጠቃላይ በመስኮት ደረጃ ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት የሚሰጡ ቅርንጫፎች ቁጥርም 1,623 ደርሷል፡፡ በ2020/21 የመጀመሪያ ስድስት ወራት፡-

- ከተለያዩ የሲቢኢ ኑር የቁጠባ ሂሳብ አይነቶች 9.8 ቢሊዮን ብር ተቀማጭ ገንዘብ መሰብሰብ የተቻለ ሲሆን፣ ይህ ክንውን የዕቅዱን 266 ከመቶ ነው፡፡ በዚህ መሰረት የግማሽ አመቱ የሲቢኢ ኑር አጠቃላይ ተቀማጭ 42.3 ቢሊዮን ብር ደርሷል፡፡
- በግማሽ አመቱ 483 ሺህ አዳዲስ የሲቢኢ ኑር ደንበኞች ሂሳብ የከፈቱ ሲሆን፣ የአገልግሎቱን ደንበኞች ቁጥርም 3.3 ሚሊዮን ደርሷል፡፡
- በግማሽ አመቱ ከሲቢኢ ኑር ፋይናንስ ከቀረበላቸው ደንበኞች 543.7 ሚሊዮን ብር ተመላሽ የተሰበሰበ ሲሆን፣ 1.96 ቢሊዮን ብር አዲስ ፋይናንስ ማቅረብ ተችሏል፡፡ በአሁኑ ጊዜ የሲቢኢ ኑር አጠቃላይ ፋይናንስ የተደረገ የገንዘብ መጠን 4.7 ቢሊዮን ብር ደርሷል፡፡

## 8. ማህበራዊ ኃላፊነትን ለመወጣት የተደረጉ ድጋፎች

የኢትዮጵያ ንግድ የህብረተሰቡን ማህበራዊ ችግሮች ለማቃለል የሚያግዙ ፕሮጀክቶችን በገንዘብና በቁሳቁስ በመደገፍ ተቋማዊ የማህበራዊ ኃላፊነቶቹን በከፍተኛ ደረጃ እየተወጣ ይገኛል። ለዚህ አገልግሎት የሚውል ከፍተኛ መጠን ያለው በጀት በዕቅድ የሚያዝ ሲሆን፣ በተለያዩ አጋጣሚዎች እንደተስተዋለውም በሀገሪቱ ውስጥ ለሚከሰቱ ድንገት ደራሽ ጉዳዮች ድጋፍ በማድረግ የሀገር ደራሽ መሆኑን አሳይቷል፡፡

በ2020/21 የመጀመሪያ ግማሽ አመትም ማህበራዊ ኃላፊነትን ከመወጣት አንፃር በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

- በዚህም ባለፉት ስድስት ወራት ከ1.2 ቢሊዮን ብር በላይ ድጋፍና እርዳታ በማድረግ የህዝብ አጋርነቱን አሳይቷል፡፡
- የአካባቢ እንክብካቤን ዋና የባንኩ ትኩረት ከማድረግ አንፃር በየአመቱ የሚከናውን ሲሆን በዚህ ግማሽ አመትም በመላ ሀገሪቱ ከ1 ሚሊዮን በላይ የተለያዩ የፍራፍሬና የዛፍ ችግኞች ተከላ ተከናውኗል፡፡
- የባንኩ የሥራ አመራርና ሠራተኞችም የደም ልገሳ አድርገዋል፡፡

## 8. ሌሎች ክንውኖች

- የባንኩን አገልግሎት ለማዘመን፣ የ2025 ራዕያችንን ለማሳካትና የአገልግሎት ጥራት ላይ መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችሉ በርካት የኢንፎርሜሽን ሲስተም ፕሮጀክቶች ታቅደው በክንውን ላይ ይገኛሉ፡፡ ተጠናቀው ወደስራ የገቡ ፕሮጀክቶች ያሉ ሲሆን፣ ሌሎች በተለያየ የክንውን ደረጃ ላይ ይገኛሉ፡፡
- አለም አቀፍ ስጋት የሆነውን የኮቪድ-19 ወረርሺኝ ከመከላከል አንፃር 10 ሺህ ለሚጠጉ የባንኩ ሠራተኞች ምርመራ ተደርጎላቸዋል፡፡
- የባንኩን ዋና መ/ቤት ህንፃ ጨምሮ ከ18 በላይ የቅርንጫፍ እና የዲስትሪክት ቢሮ ህንፃ ግንባታዎች በተለያዩ የሀገሪቱ ከተሞች እየተከናወኑ ሲሆን፣ የግንባታ ሂደታቸውም በተለያየ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ በተለይ የባንኩ ዋና መ/ቤት ግንባታ በተቻለ መጠን የማሳመሪያ ስራዎች አጠናቆ ለማስመረቅ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

## 9. ማጠቃለያ

ባጠቃላይ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የባንኩን የ2025 ራዕይ ከማሳካት አንጻር እንዲሁም የሀገራችንን የፋይናንስ ዘርፍ ለማሳደግና የክፍያ ሥርአቱን ለማዘመን የሚረዱ የተለያዩ እቅድና ፕሮጀክቶችን በመንደፍ ተግባራዊ ያደረገ ሲሆን የተገኘውም ውጤት አበረታች ነበር፡፡ በተለይ ኮቪድ-19 እና ሌሎች በየአካባቢው የነበሩ አለመረጋጋቶች በቢዝነስ እንቅስቃሴው ላይ ካሳደሩት ተጽእኖ አንፃር የተገኘው ውጤት አበረታች ነው፡፡ በአንዳንድ የአፈጻጸም ዘርፎች የነበሩ ጉድለቶችን በቀጣይ ግማሽ አመት በአግባቡ ለመሙላት በባንኩ በኩል ዝግጅቶች ተደርገዋል፡፡